# ጀግናችን

ዘውዲቱ የማነ

2019-11-03

እ ግዚአብሔር ከፊቱ፣ ቀድሞ እየደረሰ

ስ ንቱ መንጋ ሲዝት፣ ጀግናው ገሰገሰ።

ከ ፉ ሊያጠፋው ሲል፣ በእምነቱ የዳነ

ን ፁህ ሀቀኛ ነው፣ ለእግዜር የታመነ።

ድ ርድር አያውቅም፣ በሰብዓዊነቱ

ር ጋታው ድንቅ ነው፣ ፅናቱ ብርታቱ።

ነ ፃነት የሚሻ፣ ለሰው ልጅ በሙሉ

ጋ ጠ ወጥ አይደለም፣ አይልም ግደሉ።

ነ ገም ይደግፈው፣ አምላክ በሄደበት

ው ል ያለው ጀግና ነው፣ ጠላት የበዛበት።